# ጓደኝነትና ዕድል

ደውሎ ሲነግረኝ የሚቀልድብኝ ነበር የመሰለኝ አብነት ፀጋዬ ነው ይህን የተናገረው አብነት ፀጋዬና ፍቃዱ ተስፋዬ ወጣቶች ናቸው፡፡ አብነት 30 ዓመት ሲሆነው ፍቃዱ ደግሞ 27 ዓመት ሞልቶታል፡፡ አብነት የዛሬ 5 ዓመት ገደማ እንጀራ ፍለጋ ወደ ሻሸመኔ በመሄድ ትንሽዬ መለዋወጫ መሸጫ ሱቅ ይከፍታል፡፡ በዚያው ዓመት አብነትና ፍቃዱ የጓደኝነት መሰረት ይጥላሉ፡፡ ወዳጅነታቸው እየጠነከረ ይሄዳል፡፡

በህዳር ወር በአንደኛው ቀን ለምን ሻይ ቡና አንባባልም ይሉና አንዲት ካፍቴሪያ ይገናኛሉ፡፡ ሻይ ቡና እያሉም ፍቃዱ ህዳር 30 2003 የሚወጣውን አንድ ልዩ ሎተሪ ነጠላ ቲኬት ይገዛል፡፡ አብነት ደግሞ ፈጣን ይፍቃል፡፡ ከፋቀው ፈጣን ሎተሪ 5 ብር ያገኛል፡፡ እሱም በተራው ፍቃዱ ቆርጦት ያስቀራትን የልዩ ሎተሪ ይቆርጣል፡፡

ፍቃዱ የባጃጅ ሹፌር ነው ፡፡ቀድሞ ማውጫውን የተመለከተው ፍቃዱ አብነት ዛሬ የምስራች ልነግርህ ነው ይለዋል ፡፡




"ምስር ብላ ምን ተገኘ" ሲለው

"ደረሰን እኮ ይለዋል"

"ምኑ "

"ልዩ ሎተሪ ነዋ አትቀልድ እንጂ"

"እውነቴን ነው" ይለዋል፡፡

ፍቃዱና አብነት ተገናኝተው እንደገና ማውጫውን ሲመለከታሉ በ3ኛ ዕጣ የ350,000 ብር ደርሷቸዋል፡፡

አብነት አሁን የመኪና መለዋወጫ ሱቁን ሰፋ ለማድረግ አስቧል፡፡ ፍቃዱም እነደዚሁ በተሸለ ስራ ለመሰመራት ቋምጠወል፡፡

አንደቸው ለአንዳቸው እንዴት እንደሚጨነቁ ለመጥቀስ ያህል አብነት በተፈጥሮው አይነአፋር ብጤ ነው ማለት ይቻለል፡፡ ይህ አይነ አፋርነቱን የተገነዘበው ፍቃዱ

ቃለመጠየቅ ባደረግነለቸው ወቅት ቶሎ ቶሎ ምለሽ ይስጥ የነበረው እሱ ነበር፡፡ አብነትና ፍቃዱ በልዩ ሎተሪ ተመሳሳይ ታሪክ ጽፈዋል፡፡ በአንድነት በተመሳሳይ ቁጥር የአንድ ዕድል ተቋዳሽ ሆነዋል፡፡ ይህም ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ዕድል ያልነጣጠላቸው ጓደኞሞች ሆነዋል፡፡ ጓደኙነት እንዲህ ሲሰምር ደስ ይላል፡፡